DEPARTMENT OF ENERGY & ENVIRONMENT | GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# የከተማ ግብርና የከተማ ግብርና የግብር ማቅለያ ቢሮ ፕሮግራም እና ማመልከቻ

ይህ ማመልከቻ የቀረበው ለዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የከተማ ግብርና ቢሮ (OUA) የከተማ ግብርናየግብር ማቅለያ (UFTA) ፕሮግራም ነው፣ በዲሲ ኦፊሻል ኮድ §47-868 "ለተወሰኑ የከተማ እርሻዎች የግብር እዳ ቅናሽ" ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሃይል አቅርቦት እና የአካባቢ ጥበቃ መምሪያ (DOEE) ስር።

የ UFTA ፕሮግራም እንደ ከተማ እርሻ በተከታታይነት ጥቅም ላይ ለዋሉ ሪል ፕሮፐርቲ ግብሮች **እስከ 90% በመቶ የግብር ማቅለያ**ን ለንብረት ባለቤቶች ያቀርባል።

> **"የከተማ ግብርና "** ማለት ለትርፍ፣ ትርፍ ላለሆነ፣ ወይም ለትምህርታዊ ዓላማዎች ሰብሎችን ለማሳደግ፣ ለማልማት፣ በፋብሪካ ውስጥ አስገብቶ ለማምረት፣ እና ለማሰራጨት በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ጥቅም ላይ የዋለ ማንኛውም ንብረት ማለት ነው። (የD.C. ኦፊሴሊያዊ ኮድ § 48-401 (4))

የከተማ ግብርናው ምርትን ማሳደግ እና የዲስትሪክቱን የተከታታይ DC 2.0 ግቦችን ለማሳካት ማገዝ አለበት። ማቅለያው እንዴት እንደሚወሰን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ከታች ያለው "የግብር ማቅለያዎን ማስላት" የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።

## እባክዎ እነዚህን መመሪያዎች በጥንቃቄ ያንብቡ እና ይከተሉ

- የማመልከቻውን ማንኛውም ክፍል አያስወግዱ ወይም አይቀይሩ።
- ሁሉንም ክፍሎች ይሙሉ።
- ጥያቄው የማይመለከትዎ ከሆነ፣ "n/a" ላይ ምልክት ያድርጉ።
- ቅጹን በትክክል ይሙሉ እና ሁሉም መልሶችን ዳግም ያረጋግጡ።
- ስሌትዎን ለማረጋገጥ ሁሉም የተጠየቁ የስኩዌር ፉቴጅ ልኬቶችን ለ DOEE ያቅርቡ። እንዲሁም እንደ እርሻ ጥቅም ላይ የዋለውን የንብረት መቶኛ በትክክል ማስላትን እርግጠኛ ይሁኑ። ይህ፣ የእርሻ አጠቃቀም ዓመታዊ የመጀመሪያ እና የማብቂያ ቀኖች ጋር፣ የግብር ማቅለያ መጠንዎን ለመወሰን ጥቅም ላይ ይውላል።

## ለUFTA ማመልከቻ የሚያስፈልጉ ሰነዶች

- ☐ የተሞላ የ UFTA ፕሮግራም ማመልከቻ ቅጽ (ከታች)።
- ☐ የከተማ ግብርና እና ማንኛውም መዋቅሮች ልኬቶችን የሚያሳይ ቀላል የንብረት የቦታ ካርታ።
- ☐ እንደ ከተማ ግብርና ቦታ በተከታታይነት ጥቅም ላይ የዋለውን የንብረት ክፍል ሶስት እስከ አራት(3-4) የቀለም ፎቶግራፎችን። ፎቶግራፎቹ ነባር ሁኔታዎችን እና የከተማ ግብርና ቦታ ይዘትን ከሌላ ማንኛውም የንብረቱ ክፍሎች ጋር በማነጻጸር ለማሳያት በቂ እንደሆኑ ያረጋግጡ።
- ☐ ዝርዝር መግለጫ (በከፍተኛ 500 ቃላት) የከተማ እርሻው ***ቀጣይነት ያለው እና እኩልነት ያለው*** የምግብ ሥርዓትን እንዴት እንደሚያስተዋውቅ እና እንደሚያሳድግ የሚያሳይ መግለጫ።
- ☐ በማቅለያ ፊስካል ዓመት የከተማ እርሻ ላይ ለተመረቱ ለእያንዳንዱ ለሚመረት ሰብል የሚታሰበው ጠቅላላ የሰብል ምርትን የሚያካትት የአንድ (1) ዓመት የመትከል እቅድ።

ሁሉንም የተጠየቁ መረጃዎችን እና ሰነዶችን በማቅረብ ማመልከቻዎን በኢሜይል ወይም በፖስታ ያስገቡ፣ ለ፥


ኬት ሊ
Kate.lee@dc.gov
የከተማ ግብርና ቢሮ
የዲሲ የሃይል አቅርቦት እና
የአካባቢ ጥበቃ መምሪያ
1200 First Street NE, 5th
Floor
Washington, DC 20002

### የUFTA ማመልከቻ ግምገማ

የ UFTA ፕሮግራም ማመልከቻዎ አንዴ ከደረሰ በኋላ፣ OUA ለብቁነት ይገመግም እና ይመዝናል። ንብረትዎ ብቁ እንዳልሆነ OUA ከወሰነ፣ በ 30 ቀናት ውስጥ እንዲያውቁ ይደረጋል። ንብረትዎ ለመሳተፍ ብቁ ሊሆን እንደሚችል OUA ከወሰነ፣ OUA የ UFTA ማመልከቻ ላይ ያለውን መረጃ ለማረጋገጥ እና በታቀዱ ቀናት ወቅት የከተማ ግብርና ተከታታይ አጠቃቀምን ለማረጋገጥ ለቦታ ጉብኝት ቀጠሮ ይይዛል። ከተረጋገጠ፣ OUA የ UFTA ፕሮግራም ማመልከቻዎን ያጸድቃል፣ እና ወደ Office of Tax Revenue (የግብር ገቢ ቢሮ) (OTR) ለተፈጻሚነት ይላካል። OTR የማቅለያ መጠንን ሲያረጋግጥ፣ OUA የግብርና ቦታ ለግብር ማቅለያ ያዋጣውን የዶላር ($) መጠን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ለገበሬው ያቀርባል።

### የUFTA ፕሮግራም የገንዘብ ድጋፍ አጠቃላይ እይታ

- ለእያንዳንዱ ቦታ ሊፈቀድ የሚችል ዓመታዊ የግብር ማቅለያ መጠን በከፍተኛ ለ $20,000 ($10,000 በግማሽ ዓመት) ወይም እንደ ከተማ ግብርና በተከታታይነት ጥቅም ላይ ለዋለው የንብረት ክፍል የተጨባጭ ንብረት ግብሮች እስከ 90 በመቶ የግብር ማቅለያ ላይ ተደርጓል፣ ከሁለቱ የሚያንሰውን።

- ላሉ የተረጋገጡ ንብረቶች ለማንኛውም የግብር ዓመት የሚቀል ግብር መጠን ካለው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ፣ ያሉ ገንዘቦች ለሁሉም ንብረቶች በተመጣጣኝ ይመደባሉ።

### የግብር ማቅለያዎን ማስላት

በ UFTA ስር፣ የንብረት ባለቤቶች ግብርናቸው የሚሰራበት የግብር ጊዜያት ወቅት ለከተማ ግብርና ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ የመሬት ክፍሎች ላይ እስከ 90 በመቶ የንብረት ግቦቻቸው ተቃሎ መቀበል ይችላሉ። መሬቱ በ100 በመቶ ለከተማ ግብርና ከዋለ፣ እንግዲያውስ እስከ 90 በመቶ የንብረት ግብሮቹ የሚቃለሉ ይሆናል። መሬቱ 50 በመቶ ለከተማ ግብርና ከዋለ፣ እንግዲያውስ እስከ 45 በመቶ የንብረት ግብሮቹ የሚቃለሉ ይሆናል (የ 90%ቱ 50% የሚመጣው 45% ስለሆነ)። በሌላ አነጋገር፣ በዚህ ማቅለያ ስር፣ የንብረት ባለቤት ለከተማግ ብርና የዋለ መሬት ላይ እስከ 10 በመቶ የሚያንስ የንብረት ግብር ሊከፍል ይችላል። አመልካቾች ግብርናው በተከታታይ ጥቅም ላይ የዋለበትን ጊዜ እንዲያረጋግጡ ይጠየቃሉ፣ በዝቅተኛው የሚመለከተው የግብር ጊዜ ቢያንስ ሶስት (3) ወራትን ማካተት ያለበት።

የከተማ ግብርና እየተሰራ ያለው ግንባታ ውስጥ ወይም በንብረቱ ላይ እየተስተካከለ ያለው የመሬት ክፍል ላይ የሚደረግ ከሆነ፣ የንብረት ግብሩ ለከተማ ግብርና ብቻ የዋለ የመሬት ክፍል ነው የግብር ሊቀል የሚችለው። ህንጻው ወይም እየተስተካከለ ያለው ለግብርና ብቻ የማይውል ከሆነ፣ ማቅለያው ለግብርና ብቻ የዋለው የተስተካከለው ክፍል ላይ ተግባራዊ ይሆናል። ማለትም፣ ግብርናው የብዙ ፎቅ ህንጻ ጣሪያ ላይ የሚደረግ ከሆነ፣ ማቅለያው ተግባራዊ የሚሆነው የጣሪያ ላይ አትክልት ቦታ ግብርናስኩዌር ፋቴጅን ለህንጻው ጠቅላላ ስኩዌር ፋቴጅ (ሁሉም መሬቶችን ጨምሮ) በማካፈል የሚገኘው ላይ ነው።

የውሸት መረጃን ማቅረብ ቅጣት $1,000 በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት፣ የ180 ቀናት ያልበለጠ እስራት፣ ወይም ሁለቱም፣ በዲሲ ኦፊሴሊያዊ ኮድ § 22-2405 እንደሚያስገድድ። በውሸት መሃላ ቅጣት $2,500 የማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት፣ ሶስት (3) ዓመት ያልበለጠ እስራት፣ ወይም ሁለቱም፣ በዲሲ ኦፊሴሊያዊ ኮድ § 22-2404 እንደሚገያስድድ ተቀምጧል።።